# የሃገሪቷ ወቅታዊ
# የደህንነት ስጋት ትንተና

## (ለጠ/ሚ ዶር አብይ አህመድ የቀረበ ምስጢራዊ ሰነድ)

አዘጋጅ ፕ/ር ብርሃኑ ነጋ
አንዳርጋቸው ፅጌ

ሚያዝያ 2013 / April 2021

# ማውጫ


ገጽ

መግቢያ ........ 1

**ክፍል አንድ፡ ወቅታዊ የብሄራዊ ደህንነት ስጋቶች** ........ 1

1. የሃገር ውስጥ ተጨባጭ የደህንነት ስጋቶች ........ 1

1.1. እየተራዘመ የመጣው በትግራይ ያለው ጦርነት........ 1

1.2. መንግስትን በሃይል ለመጣል የሚደረግ እንቅስቃሴዎች........ 3

1.2.1. ህወሃት ........ 3

1.2.2. የኦነግ (የኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት) ........ 4

1.2.3. የአማራ ሰራዊት (የፋኖ ሰራዊት) ........ 4

1.3. የብልጽግና ችግሮች ........ 5

1.3.1. የአማራ ብልጽግና ........ 5

1.3.2. የኦሮሚያ ብልጽግና ........ 6

1.4. ጽንፈኝነት ........ 7

1.5. የደህንነት ማህበረሰብ እና የጸጥታ ተቋማት አቅም ደካማነት ........ 9

2. የውጪ ተጨባጭ የደህንነት ስጋቶች ........ 9

2.1. ግብጽ የፈጠረችው ስጋት ........ 9

2.2. ሰሜን ሱዳን የፈጠረችው ስጋት ........ 10

**ክፍል ሁለት፡ የምርጫ ደህንነት** ........ 10

**ክፍል ሶስት፡ ኢዜማ ሊከተላቸው የሚገባቸው ከብሄራዊ ደህንነት ጋር የተያያዙ አቅጣጫዎች** ........ 12

**ክፍል አራት፡ መንግስት ሊተገብራቸው የሚገቡ ምክረ ሃሳቦች** ........ 13

**የሃገሪቷ ወቅታዊ የደህንነት ስጋት ትንተና**

**መግቢያ**

ሃገራችን በአሁኑ ሰአት ከፍተኛ እና ውስብስ የብሄራዊ ደህንነት ስጋቶች እና አደጋዎች ተጋርጠውባት ይገኛል። በተለያየ ደረጃ እና መልክ ሊገለጽ የሚችል የደህንነት ስጋት ያለ ሲሆን በዋናነት በሃገር ውስጥ እና የውጪ የደህንነት ስጋቶች ብለን ልንከፍላቸው እንችላለን። በተለይ የውጪ የደህንነት ስጋት በሃገር ውስጥ ደህንነት ላይ የሚያሳድረው ተጽኖ ከፍተኛ መሆኑ መረሳት የለበትም። ይህ "የሃገሪቷ ወቅታዊ የደህንነት ስጋት ትንተና" በዋናነት ትኩረት የሚያደርገው ተጨባጭ የብሄራዊ የደህንነት ስጋቶች ላይ ነው። ይህን የስጋት ትንተና ለማቅረብ የተጠቀመበት የመረጃ ምንጭ የሰው መረጃ ምንጭ ሲሆን የመረጃ ምንጮችን ደህንነት ከማረጋገጥ አንጻር ጥሬ መረጃዎችን ለየብቻ አስቀምጦ የትንተናው መነሻ ምን እንደሆነ ለማሳየት አይሞክርም። በመሆኑም የመረጃ ነጥቦችን በግልጽ እንዲለዩ ተድርጎ በትንተና ውስጥ አልተቀመጠም። ይህ ትንተና 4 ክፍሎች ያሉት ሲሆን የመጀመሪያው ክፍል ዋና ዋና የሚባሉ ወቅታዊ የብሄራዊ ደህንነት ስጋቶች ነው። ሁለተኛው ክፍል ከምርጫ ደህንነት ጋር የተያያዙ ነጥቦች የሚነሱበት የምርጫ ደህንነት ጉዳዮች ሲሆን ሶስተኛው ኢዜማ ሊከተላቸው የሚገቡ አቅጣጫዎችን የያዘ ክፍል ነው። አራተኛውና የመጨረሻው ክፍል በመንግስት በኩል ሊወሰዱ የሚችሉ ምክረሃሳቦችን የያዘ ነው።

**ክፍል አንድ፡ ወቅታዊ የብሄራዊ ደህንነት ስጋቶች**

የሃገሪቷ አንድነት እና ህልውና የሚፈታተኑ ተጨባጭ የብሄራዊ ደህንነት ስጋቶች እየተከሰቱ ይገኛሉ። ይህ ተጨባጭ የብሄራዊ ደህንነት ስጋቶች የተለያየ መልክ እና ተዋንያን ያሉት ሲሆን የስጋት መጠናቸው እና አድማሳቸው በሃገሪቷ ላይ እንደሚያሳድሩት ተጽኖም የተለያየ ነው። ቀጥሎ ዋና ዋና የሚባሉ የሃገር ውስጥ ተጨባጭ የደህንነት ስጋቶች እና የውጭ ተጨባጭ የደህንነት ስጋቶችን ለየብቻ በመክፈል እንመለከታለን፡-

1. የሃገር ውስጥ ተጨባጭ የደህንነት ስጋቶች

ዋና ዋና የሚባሉ የሃገር ውስጥ ተጨባጭ የደህንነት ስጋቶች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡-

1.1. እየተራዘመ የመጣው በትግራይ ያለው ጦርነት

በትግራይ ክልል እየተካሄደ ያለው ጦርነት በህወሃት ታጣቂዎች እና በፌደራል መንግስቱ መካከል የሚካሄድ ነው። በዚህ የጦርነት ሂደት ላይ የኤርትራ ሚና ከፍተኛ ነው። በፌደራል መንግስቱ በኩል የመከላከያ ሃይል እና የኤርትራ ሰራዊት በቅንጅት ነው በህወሃት ታጣቂዎች ላይ እርምጃዎችን እየወሰዱ ያሉት። የህወሃት ታጣቂዎች የመከላከያ ሰሜን እዝ ላይ ጥቃት ሰንዝረው አብዛኛውን ሃይል የተቆጣጠሩበትና የፌደራል መከላከያ ሃይል እና የኤርትራ ሰራዊት በቅንጅት (የአማራ ልዩ ሃይል ሚና ከፍተኛ መሆኑን ሳይረሳ በተለይ ወልቃይት፣ ቃፍታ ሁመራ እና ራያ አካባቢዎች ላይ የተደረጉ ጦርነቶች ላይ በሰፊው ተሳትፏል) የመልሶ ማጥቃት እርምጃዎችን ወስደው ህወሃትን ከመቀሌ ያስወጡበት ሁኔታ እንደነበር ይታወሳል። በዚህ የጦርነት ሂደት የህወሃት የመደበኛ ውጊያ የማድረግ አቅም በከፍተኛ ሁኔታ ሊዳከም ችሏል።

ህወሃት ከክልል ስልጣን ከተወገደ በኋላ በተለያዩ አካባቢዎች የሽምቅ እና ከፊል መደበኛ የውጊያ ስልቶችን በመጠቀም ከመከላከያ እና ከኤርትራ ሰራዊት ጋር እየተዋጋ ይገኛል። የመከላከያ እና የኤርትራ ሰራዊት በጋራ በሚወስዱት እርምጃ መደበኛ

ጦርነት የማድረግ አቅም የነበረው ህወሃት አሁን ሽምቅ እና ከፊል መደበኛ የውጊያ እንቅስቃሴ ወደ የሚያደርግበት ሁኔታ ተለውጧል። የሽምቅ እና ከፊል መደበኛ የውጊያ ስልት የሚጠቀመውን የህወሃት ታጣቂዎች የፌደራል መከላከያ እና የኤርትራ ሰራዊት በሚወስዱት እርምጃ ጨርሶውኑ ማጥፋት አልቻሉም። የህወሃት ታጣቂዎች የሚንቀሳቀሱበት ነጻ የገጠራማ ቀጠናዎች አሏቸው። ከነዚህ የገጠራማ አካባቢዎች እየተነሱ የደፈጣ ጥቃቶች ይፈጽማሉ፤ የተደራጀ ዝርፊያዎችን ያከናውናሉ፤ ከፌደራል መከላከያ እና ከኤርትራ ሰራዊት ጋር አነስተኛ ውጊያዎችንም ያደርጋሉ። ይሄም የተራዘም የጦርነት ሂደት ውስጥ ሊያስገባ የሚችልበት እድል ሰፊ እንደሆነ ያሳያል።

የህወሃት ከፍተኛና ተጽኖ ፈጣሪ አካላት በቁጥጥር ስር አለመዋላቸው ወይም የእርምጃው ሰለባ አለመሆናቸው የህወሃት ታጣቂዎች በተለያዩ ቦታ ለሚያደርጉት እንቅስቃሴ ከፍተኛ የሆነ የሞራል ስንቅ ሁኗቸዋል። በተለይ በተለያዩ የትግራይ አካባቢዎች ያሉ የትግራይ ወጣቶች ወደ ህወሃት ታጣቂዎች የሚገቡ መሆኗቸው ጦርነቱን በቀላሉ እንዳይቋጭ ያደርገዋል። ህወሃት በትግራይ ወጣቶች ዘንድ ከፍተኛ ተቀባይነት ያለው ድርጅት መሆኑ እየተደረገ ካለው የውጊያ ሂደት መገንዘብ ይቻላል።

የፌደራል መከላከያ ሃይል ከኤርትራ ሰራዊት ድጋፍ ውጪ ሙሉ ትግራይን መሸፈን የሚችል አቅም የሌለው በመሆኑ በትግራይ ውስጥ የሚደረጉ የውጊያ ሂደቶችን ሙሉ ለሙሉ ለመቆጣጠር አላስቻለውም። በአሁን ሰአት ካለ የኤርትራ ሰራዊት እገዛ በመከላከያ ሃይል ብቻ የህወሃት ታጣቂዎች ላይ የሚደረገው ዘመቻ ውጤታማ የመሆን እድሉ ዝቅተኛ ነው። የኤርትራ ሰራዊት ከትግራይ እንዲወጣ በአለም አቀፍ ተቋማት እየመጣ ያለው ጫና እና የኤርትራ ሰራዊት በተራዘመ የጦርነት ውስጥ የሚገባ ከሆነ እንዲሁም ከኢትዮጵያ መከላከያ ጋር በውጊያ ስልትና አፈጻጸም ላይ የሚኖረው ልዩነት እየጎላ ከመጣ የኤርትራ ሰራዊት በትግራይ ውስጥ የሚቆይበት ጊዜ አጭር የመሆን እድል አለው። ይህም የኤርትራ ሰራዊት የኢትዮጵያ መከላከያ ሃይል እራሱን በሚገባ ሳያደራጅ ከትግራይ የሚወጣ ከሆነ ከህወሃት ጋር የሚደረገው ጦርነት ብዙ አደጋዎች ይዞ ሊመጣ እንደሚችል ይታመናል። የኢትዮጵያ መከላከያ በአሁኑ ሰአት ብቻውን ጦርነቱን ማድረግ የሚችልበት የአቅም ደረጃ ላይ ያለመሆኑ ሲታይ የህወሃት ታጣቂዎች እራሳቸውን የሚያደራጁበት እና መንግስትን የሚገዳደሩበት ሁኔታ የመፍጠር እድል ስለሚኖራቸው አካባቢው ወደ ተራዘመ የጦርነት ሁነት ውስጥ እንዲገባ ሊያደርገው ይችላል።

በትግራይ እየተካሄደ ያለው ጦርነት በንጹሃን ህዝብ ላይ እየፈጠረ ያለው የተጓዳኝ ጉዳቶች (collateral damages) ከፍተኛ መሆን የትግራይ ወጣቶች የህወሃትን የትጥቅ እንቅስቃሴ እንዲደግፉ እያበረታታቸው ይገኛል። በመከላከያ እና በኤርትራ ሰራዊት የሚፈጸሙ ኢ ሰብአዊ ድርጊቶች የትግራይ ህዝብ በፌደራል መንግስቱ ላይ ያለውን አመኔታ እየሸረሸረ ይገኛል። በመሆኑም ለህወሃት የተራዘመ የጦርነት ስልት የተመቸ ሁኔታ ይፈጥራል። የትግራይ ጊዜያዊ መንግስት በትግራይ ያለውን አጠቃላይ የቀውስ ሁኔታ በሚመጥን መንገድ እንቅስቃሴ እያደረገ አለመገኘቱና ህብረተሰቡን ከህወሃት እንቅስቃሴ ለመነጠል የሚደረገው እንቅስቃሴ ደካማ መሆን ህወሃትን የበለጠ ተጠቃሚ እያደረገ ይገኛል። በተለይ ጊዜያዊ አስተዳደሩ የቀውስ ሁኔታውን የሚመጥን አፋጣኝ እርምጃዎችን መውሰድ የሚያስችል ዝግጁነትና አቅም ባላቸው አካላት የተዋቀረ አለመሆኑና ይህ የሚፈጥረው ክፍተት ህወሃት እየተጠቀመበት ይገኛል። በጊዜያዊ አስተዳደር ውስጥ ያሉ አመራር አካላት ውስጥም ህወሃትን የሚደግፉ ሰዎች በብዛት መኖራቸው ህወሃት የመረጃ እጥረት እንዳይኖርበት አድርጓል። በመሆኑም በህወሃት ላይ የሚወሰደው እርምጃ በቀላሉ ውጤታማ እንዳይሆን ከሚያደርጉት ጉዳዮች ውስጥ አንዱ በጊዜያዊ አስተዳደሩ ውስጥ ህወሃትን የሚጠቅሙ አሻጥሮች ተጠቃሽ ናቸው።

ባጠቅላይ ከህወሃት ጋር የሚደረገው የጦርነት ሂደት በፍጥነት አለመጠናቀቁ አካባቢው ላይ ዘርፈ ብዙ ችግሮችን እያስከተለ ይገኛል። ህወሃትም እራሱን ለተራዘመ ጦርነት እያዘጋጀና የመንግስት ሃይልን በተራዘመ የጦርነት ሂደት አሽንፋለው ወደሚለው የሽምቅ እና የከፊል መደበኛ የስልት እንቅስቃሴ ውስጥ ሊገባ የቻለው። በዚህ የተራዘመ የጦርነት ስልት መንግስት ላይ ከተለያዩ አካላት ጫናዎችን እንዲፈጠር በማድረግ እና መንግስት በትግራይ እና በአካባቢው ተረጋግቶ ማስተዳደር እንዳይችል የሚያደርግ ስራዎችን በመስራት የመንግስትን ቅቡልነት ማሳጣት ዋነኛ ስራቸው ሆኗል። በተለይ የኤርትራ ሰራዊት ከትግራይ እንዲወጣ የሚያደርግ የተቀናጀ ስራዎችን በመስራት ላይ ይገኛሉ። የኢትዮጵያ መከላከያ ሃይል አቅሙን አዳብሮ ሙሉ ለሙሉ የትግራይን አካባቢ መቆጣጠር የሚያስችል ስራዎችን እስከሚሰራ ድረስ የኤርትራ ሰራዊት ቀድሞ የሚወጣበትን ሁኔታ የሚያፋጥኑ የተቀናጁ እንቅስቃሴዎችን ከሌሎች ህወሃትን ከሚደግፉ አካላት ጋር እየሰሩ ነው። በመሆኑ የኤርትራ ሰራዊት ቀድሞ የሚወጣ ከሆነ የመከላከያ ሃይልን ማሽነፍ አያቅተንም የሚል ድምዳሜ ላይ በመድረሳቸው ነው አጠቃላይ የፕሮፖጋንዳ አቅጣጫቸው የኤርትራ ሰራዊት ከኢትዮጵያ ሊወጣ የሚችልበትን ሁኔታ ላይ ተጽኖ እንዲያሳድር አድርገው እየቀረጹት ያለው።

ህወሃት በትግራይ ላይ ያለውን ከፍተኛ የመከላከያ ሃይል ክምችት ለመቀነስና ዳግም የበላይነቱን ለመጨበት እንዲያስችለው በሃገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች ስጋት እና አደጋዎች እንዲፈጠሩ ለማድረግ የሚያስችለውን ስራዎች ከወኪሎቹ ጋር እያከናወነ ይገኛል። ይህም የመከላከያ ሃይል በየአቅጣጫው እንዲበተን በማድረግ በትግራይ ላይ የሚኖረውን የምት አቅም እንዲቀንስ አድርጎ መንግስትን ወደ የተራዘመ ጦርነት ውስጥ እንዲገባ በማድረግ በተራዘመ ጦርነት ማሽነፍ የሚለውን ስልቱን የሚፈጽምበት ሂደት ነው። በመሆኑም የትግራይ ጦርነት በአጭር ጊዜ የማይጠናቀቅ ከሆነ ከኢትዮጵያ የብሄራዊ ደህንነት አደጋነት አልፎ በቀጠናው ላይ የሚያመጣው ስጋት ከፍተኛ ነው።

### 1.2. መንግስትን በሃይል ለመጣል የሚደረግ እንቅስቃሴዎች

እራሳቸውን በትጥቅ ያደራጁ እና የማደራጀት ሂደት ላይ ያሉ ሃይሎች መንግስትን በአመጽ ለመጣል እንቅስቃሴዎችን እያደረጉ ይገኛሉ። ከነእዚህ ውስጥ በብሄራዊ ደህንነት ስጋት ደረጃ የሚታዩትን ሶስት አካላት ቀጥሎ እንመለከታለን፦

#### 1.2.1. ህወሃት

ከህወሃት ጋር ተያይዞ የሚነሱ ጉዳዮችን በሰፊው ከላይ ያነሳነው ቢሆንም የህወሃት ዋነኛ አላማ ተመልሶ በሃይል የክልሉን ስልጣን መያዝ ነው። ቀጥሎም ከሌሎች ከሱ ሃሳብ ጋር ከሚዛመዱት ጋር የፌደራሉን ስልጣን መያዝ ነው። በሃገር ውስጥ የህወሃት ዋነኛው አጋር ኦነግ በተለይ እራሱን የኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት ብሎ የሚጠራው፤ መንግስት ግን ኦነግ ሸኔ የሚባለው ሃይል ነው። እንዲሁም የብሄር ድርጅቶች ህወሃት ስልታዊ አጋሩ አድርጎ ይቆጥራቸዋል። ከውጪ በኩል በዲያስፖራው የሚገኘው የትግራይ ማህበረሰብ የህወሃት ደጋፊ እንደሆነ ያምናል። የዲፕሎማሲ እና የፕሮፖጋንዳ እንዲሁም የአሻጥር ስራዎችን የሚያከናውኑ የህወሃት ዋነኛ ደጋፊዎች በዲያስፖራው አሉ። በሌላ በኩል ከውጪ መግስታት ጋር መንግስት በነበረበት ጊዜ የመሰረተው ወዳጅነት ለሚያከናውነው እንቅስቃሴ እንደሚረዳው ያምናል። በተለይ በሱዳን እና ግብጽ መንግስት ውስጥ ያሉ አካላት ጋር ባለው ወዳጅነት ምክንያት ከነዚህ አካላት ከፍተኛ ድጋፍ እንደሚደረግለት ያምናል። አንዳንድ ድጋፎችም እየተደረጉለት ይገኛል። በመካከለኛው ምስራቅ አካባቢ ካሉ ሃገሮች ጋር በቀደምት ወዳጆቹ አማካኝነት አዲስ ወዳጅነት ለመፍጠር እንቅስቃሴ እያደረገ እንደሆነ ይታወቃል።

ህወሃት ከዚህ በፊት አብረው ሲሰሩና በተለያየ የጥቅም አይነት ሲጎዳኙት የነበሩ ወኪሎቹን በማሰማራት በሃገር ውስጥ የተረጋጋ ሁኔታ እንዳይፈጠር እየሰራ ይገኛል። የአቢይ መንግስትን የሚያዳክም ማንኛውንም እርምጃዎች ይወስዳሉ። ኢዜማ በተለይ

ፕ/ር ብርሃኑ ነጋ ኢላማ ውስጥ ካስገቧቸው ሰዎች ውስጥ አንዱ ናቸው። በሌላ በኩል የዘውግ ጽንፈኝነት እንዲስፋፋ የሚያስችል የተቀናጀ ስራዎችን ውጪ ባለው የህወሃት መዋቅር አማካኝነት እየደገፉ ይገኛሉ። ህወሃት ኢትዮጵያ የምትባል ሃገር ጠፍታ ትግራይ የሚባል ሃገር እንዲመሰረት እና ኦሮሚያ የሚባል ሃገር እንዲኖር እንዲሁም ሌሎች ብሄሮችም ተገንጥለው የራሳቸውን ሃገር እንዲመሰርቱ የሚያስችል እቅድ አውጥቶ እየተንቀሳቀሰ ይገኛል። ባጠቃላይ ህወሃት የብሄራዊ ደህንነት ተቀዳሚ ስጋት ነው።

### 1.2.2. የኦነግ (የኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት)

የኦነግ ዋና አላማ ኦሮሚያ የሚባል ሃገር መመስረት ነው። ይህ የማይቻል ከሆነ ኮንፈደሬት የሆነ ኦሮሚያን በኢትዮጵያ ውስጥ ማምጣት ነው። ኦነግ በዋናነት በምእራብ ወለጋ እና በጉጂ/ቦረና አካባቢ ይንቀሳቀሳል። በአሁን ሰአት እራሱን በገንዘብ፣ በሰው ሃይል እና በመሳሪያ እያደራጀ ይገኛል። ይህን አቅም በዋናነት ከህወሃት፣ በአካባቢው ሃገራት ካሉ ቡድኖች፣ ከህዝቡ እና ከባለሃብቶች ነው የሚያሰባስበው። በተለይ በመንግስት መዋቅር ውስጥ ያሉ የመንግስት አካላት የመረጃ እገዛ ያደርጉለታል። የመንግስት የታችኛው መዋቅር ለኦነግ አላማ የመጠቀም አቅሙ ከፍተኛ ነው። በህብረተሰቡ ላይ የሚወስዳቸው አሰቃቂ እርምጃዎች ህዝቡ የሚደርስልኝ የለም በማለት ከኦነግ ጎን እንዲሰለፍ እያደረገው ነው። በሚንቀሳቀስበት ቦታዎች የወጣቱ ድጋፍ አለው። ጠላት ብሎ የሚጠራውን የአቢይ አስተዳደር ለማስወገድ ብሎውም በኦሮሚያ ላይ የበላይነትን ለማኘየት በሚል ነው የሚንቀሳቀሰው።

ኦነግ የብሄር ድርጅቶች እንደ አጋር አድርጎ የሚወስድ ሲሆን የአንድነት ድርጅቶችን እንደ ኢዜማ እና ብልጽግና ያሉትን ድርጅቶች መጥፋት አለባቸው ብሎ ያምናል። ብልጽግና የነፍጠኛ ስርአት አቀንቃኝ ነው ብሎ ከኢዜማ ጋር መድቦታል። በመሆኑም የብልጽግና ካድሬዎች ከኦነግ ጋር የማይተባበሩ ከሆኑ እርምጃ ሊወሰድባቸው ይገባል ብሎ በቻለው አቅም እርምጃዎችን እየወሰደባቸው ይገኛል።

የኦነግ የመሳሪያ አቅርቦት ፍላጎቱን ከመንግስት ጋር በሚያደርገው ውጊያ ማርኮ የሚያገኘው አንዱ ሲሆን ከመንግስት ውስጥም በአሻጥር የሚያቀርቡለት አሉ። በባለሃብቶች በኩልም የመሳሪያ ግዢ የሚፈጸምለት ጊዜም አለ። በሌላ በኩል በዘረጋው መረብ አማካኝነት ደቡብ ሱዳን እና ሰሜን ሱዳን ውስጥ ካሉ ቡድኖችም መሳሪያዎች ይቀርብለታል። ባጠቃላይ ኦነግ የብሄራዊ ደህነት ስጋት ከሆኑ ዋነኞች ውስጥ አንዱ ነው።

### 1.2.3. የአማራ ሰራዊት (የፋኖ ሰራዊት)

በአማራው ላይ በተለያየ ጊዜ የሚፈጠሩ ግድያዎችና መፈናቀሎች ሆን ተብሎ በአቢይ አስተዳደር አማራውን ለማዳከም የሚከናወን ነው በሚል እና አማራውን ከማንኛውም ጥቃት መከላከል ይኖርብናል በማለት የህቡዕ እንቅስቃሴዎችን ለማድርግ የሚያስችል የህቡዕ መዋቅሮች እየተዘረጉ ነው። ይህ የህቡዕ እንቅስቃሴ የአማራ ሰራዊት ወይም የፋኖ ሰራዊት የሚል ስያሜ የተሰጠው ሲሆን ዋና አላማው አማራ ክልልን በመያዝ ከኦሮሞ ብልጽግና ተጽኖ ማላቀቅ የሚል ነው። ይህ የህቡዕ እንቅስቃሴ የፋኖነት አደረጃጀት በተለያዩ አካባቢዎች በመመስረት ህዝባዊ አመጽ በክልሉ ላይ እንዲኖር እና ክልሉን ለመቆጣጠር የሚያስችል ዝግጁነት ለመፍጠር የሚደረግ ነው።

በሰሜን ሸዋ፣ በጎጃም እና በወሎ አካባቢ የተደራጀ የህቡዕ እንቅስቃሴ የሚያደርጉ ዝግጅቶች እና ውይይቶች ተከናውነዋል። በህቡዕ ለተደራጁ ሰዎች ስልጠናዎችን ለመስጠት የሚያስችሉ ዝግጅቶች እየተደረጉ ይገኛሉ። የእነዚህ የተደራጁ ሃይላት

በአማራ ብልጽግና ውስጥ ያሉ የተወሰኑ የመንግስት ሰዎች ድጋፍ ያላቸው ሲሆን በአብን (የአማራ ብሄራዊ ንቅናቄ) ውስጥ ያሉ የተወሰኑ ግለሰቦች በእንቅስቃሴው ዙሪያ ይገኛሉ።

በዚህ እንቅስቃሴ ዙሪያ ያሉ ግለሰቦች የአማራ ብልጽግና ውስጥ ያሉ አመራሮችንን እነሱ ወደሚፈልጉት መንገድ እንዲመጡ ማድረግ አንዱ ስልታቸው ሲሆን እንቅስቃሴዎቻቸውን የሚቃወሙና እንቅፋት የሚሆኑ ካሉ እስከ ማስወገድ ድረስ የሚሄድ ዝግጅት መፍጠር እንደሚገባ ስምምነት አላቸው። የዚህ እንቅስቅሴ ሌላው ኢላማ ኢዜማ ሲሆን ኢዜማ ውስጥ ያሉ ግለሰቦችን በተቻለ መጠን የተወሰኑትን መያዝና የድርጅቱን መዋቅር ሙሉ ለሙሉ ማፍረስ የሚል ይገኝበታል። በዚህ ሂደት የሚያስቸግሩ አካላት ካሉ እስከ ማስወገድ የሚደርስ እርምጃዎች ሊወሰድባቸው ይገባል ይላሉ። ባጠቃላይ ይሄ የህቡእ እንቅስቃሴ በዋናነት የአማራ ብልጽግናን በመቆጣጠር አማራ ክልልን ወደ ሚፈልጉት አቅጣጫ ለመውሰድ ነው እየሰሩ የሚገኙት። በአሁን ሰአት በዝግጅት ደረጃ እና በመለስተኛ እንቅስቃሴዎች ያሉ ቢሆንም አካባቢውን ትርምስ ውስጥ እንዲገባ የማድረግ አቅም ያለው በመሆኑ ከብሄራዊ የደህንነት ስጋት ውስጥ አንዱ ተደርጎ ይወሰዳል።

### 1.3. የብልጽግና ችግሮች

ብልጽግና ገዢው መንግስት ነው። በብልጽግና ውስጥ ወጥ የሆነ የአስተሳሰብ አንድነት የለም። በተለይ በአማራ እና ኦሮሚያ ብልጽግና መካከል የእርስ በእርስ መመላለሶች ይታያሉ። በአፋር እና በሶማሌ ብልጽግና መካከልም ችግሮች አሉ። በአማራ እና ቤንሻንጉል ጉምዝ ብልጽግና መካከልም አለመግባባቶች አሉ። በደቡብ እና ሲዳማ መካከል እስካሁን ያልተፈቱ ጉዳዮችም አሉ። ብልጽግና አንድ ወጥ ፓርቲ ነኝ ቢልም የተለያዩ ፍላጎት ባላቸው አካላት የተዋቀረ ፓርቲ መሆኑ እሙን ነው።

በብልጽግና የሚፈጠሩ ችግሮች የገዢው ፓርቲ እንደመሆኑ በሃገር ላይ የሚያሳድረው ተጽኖ ከፍተኛ ነው። አንዳንድ ችግሮቹ ቀጥታ የብሄራዊ ደህንነት ስጋት የሚሆኑበት ሁኔታም አለ። በተለይ ብልጽግና ውስጥ የሚፈጠር ክፍፍል በጸጥታ ተቋማት ውስጥ የሚኖረው ተጽኖ ከፍተኛ በመሆኑ ትልቅ አደጋን ይዞ የሚመጣበት ሁኔታ እንዳለ ሊታሰብ ይገባል።

በብልጽግና ውስጥ የአቢይን አመራርነት የማይቀበሉ አካላት አሉ። እነዚህ አካላት በኦሮሚያ እና አማራ ብልጽግና ውስጥ ይገኛሉ። ሁለቱ አካላት የአቢይ አመራርን የማይቀበሉበት የየራሳቸው ምክንያት አላቸው። የአማራ እና የኦሮሚያ ብልጽግና ያሉባቸውን ጉዳዮች ለየብቻ እንመልከት፡-

#### 1.3.1. የአማራ ብልጽግና

የአማራ ብልጽግና ወጥ የሆነ አመራር የለውም። እርስ በእርሱ የተከፋፈለ ነው። በፌደራል እና በክልል ባሉ ባለስልጣናት መካከል የተለያዩ ልዩነቶች አሉ። እንዲሁም በክልሉ ውስጥም በተለያዩ ቡድኖች ተከፋፍለው አንዱ ሌላውን ይጠባበቃል። የክልሉ መስተዳደር እርስ በእርሱ የሚናበብና ወጥ የሆነ አመራር መስጠት አልቻለም። በተለይ የአማራ ማንነት ባላቸው ህዝብ ላይ በተለያዩ ቦታዎች የሚደርሱ ግድያዎች እና መፈናቅሎች የክልሉ አብዛኛው አመራር የኦሮሚያ ብልጽግናን ተጠያቂ ያደርጋል። በዚህ ምክንያት በአቢይ አመራር ላይ ከፍተኛ ቅሬታዎችን ያቀርባሉ። አንዳንዶች አቢይ ሃገሪቷን መምራት አልቻለምና ከስልጣኑ መነሳት አለበት የሚሉ አቋሞችን ሲያራምዱ ይታያል።

ክልሉ የአማራ ብሄርተኝነትን በሚገፉ አክቲቪስቶች፣ ባለሃብቶች እና የተለያዩ ፍላጎት ባላቸው አካላት በቀላሉ ተጽኖ ውስጥ ሲወድቅ ይታያል። በተለይ አክቲቪስቶች እና ባለሃብቶች በክልሉ የመንግስት መዋቅር ላይ ከፍተኛ ሚና አላቸው። የተለያዩ የክልሉ አመራሮች የእራሳቸውን ስልጣን ለማደላደል እነዚህን አካላት በመጠቀም ስልጣናቸውን ለማደላደል ሲጥሩ ይታያሉ።

የአብን ደጋፊ የሆኑና በክልሉ የመንግስት መዋቅር ውስጥ የሚገኙ አካላት ሌላው በክልሉ ውስጥ ያሉ ጉዳዮችን ውስብስብ እንዲሆን በማድረግ የራሳቸውን ሚና ይወጣሉ።

ክልሉ ከወልቃይት እና ራያ ጋር ተያይዞ ያሉ ጉዳዮችን በሚፈልገው መልኩ ማስኬድ ባለመቻሉ ከፍተኛ ውጥረት ውስጥ ይገኛሉ። ይሄም ከፌደራሉ መንግስት ጋር በአካሄድ ላይ እንዳይግባቡ አድርጓቸዋል። የክልሉ አስተዳደርን አቶ አገኘሁ ተሻገርን ከክልሉ ስልጣን ላይ ለማንሳት የተለያዩ እንቅስቃሴዎች ሲደረጉ ቆይተዋል። እስካሁን ውጤታማ ባይሆንም እሱን ለማንሳንት ከሃይል ጋር የተቀላቀለ እንቅስቃሴ ውስጥ የሚገባ ከሆነ ክልሉን ለሌላ ዙር ትርምስ ሊዳርግ የሚችልበት እድል አለ።

የክልሉ የአመራር አካላት በአካባቢያዊነት ተቧድነው በክልሉ ውስጥ እርስ በርስ ሲጓተቱ ማየት የተለመደ ነው። ይሄ መጓተተ ሄዶ ሄዶ የጸጥታ አካላትን ወደ የሚያሳትፍ እንቅስቃሴ አድጎ ክልሉን የትርምስ ማዕከል እንዳያረግ ስጋት አለ። በክልሉ ውስጥ ያሉ አመራሮች በፌደራል የስልጣን እርከን ላይ ያሉ የአማራ ብልጽግና አመራሮችን የአማራን ጥቅም እያስጠበቁ አይደለም በሚል ብልጭ ድርግም የሚል የአለመግባባት ጉዳዮች በተደጋጋሚ ሲነሳ ሰንብቷል። ይሄም በፌደራሉ እና በአማራ ክልል ባለስልጣናት መካከል የእርስ በርስ ሽኩቻ እንዳይጀመር ያሰጋል። በተለይ በአማራ እና ኦሮሚያ ብልጽግና አመራሮች መካከል የሚታየው አለመግባባት እየሰፋ ሄዶ ወደ ሃይል እንቅስቃሴ እንዳያመራ ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ የሚያስፈልግበት ጊዜ ላይ መሆኑን መታወቅ ይኖርበታል። በሁለቱ መካከል የሚታየው ውጥረትና ውጥረቱን ተጠቅሞ የፖለቲካ ድጋፍ ማግኛ ለማድረግ የሚደረገው ጥረት ሌላ የደህንነት አደጋ ይዞ የመምጣት እድሉ ከፍተኛ ነው።

### 1.3.2. የኦሮሚያ ብልጽግና

የኦሮሞ ብልጽግና እንደ አማራ ብልጽግና ወጥ የሆነ አመራር የለውም። በተለይ የታችኛው መዋቅር የላይኛው አመራር የሚያስተላልፈውን መመሪያ ሙሉ ለሙሉ የመተግበር ፍላጎት የለውም። የታችኛው መዋቅር ከራሱ ፍላጎት ጋር የሚቃረንን መመሪያ እንዳላየ ሲያልፍ በተደጋጋሚ ይታያል። የኦነግ ሸኔ እንቅስቃሴን ምክንያት በማድረግ የታችኛው መዋቅር የላይኛውን አመራር የሚያስተላልፈውን ትእዛዝ በተደጋጋሚ በዝምታ ወይም ምንም አይነት እንቅስቃሴ ሳያደርግ እንደሚያልፈው ለመታዘብ ተችሏል።

የኦሮሚያ ብልጽግና ውስጥ የእነ ጃዋር እና ኦነግ ሸኔ ደጋፊዎች በብዛት በመንግስት መዋቅሩ ውስጥ ያሉ መሆናቸው ወጥ የሆነ ድርጅታዊ ቅርጽ እንዳይይዝ አድርጎታል። እንዲሁም የአቢይ አስተዳደርን የሚቃወሙ እስከ ታችኛው መዋቅር ያሉ የመንግስት አመራር አካላት ያሉበት ነው።

በምርጫ የማይወዳደሩ የኦሮሞ ብልጽግና አመራሮች ተጽኖ በሚያሳድሩበት አካባቢያቸው ላይ የኦሮሚያ ብልጽግና መዋቅር በሚገባ እንዳይሰራ እንቅፋት የመፍጠር ፍላጎት እንዳላቸው የሚያሳዩ ጥሬ መረጃዎች ይቀርባሉ። አንዳንዱ አሉታዊ የሆነ እንቅስቃሴ ውስጥ የገቡም እንዳለ ይታወቃል።

በኦሮሞ ብልጽግና ውስጥ አቢይን በለማ የመተካት ፍላጎት ያላቸውና ጊዜ እየጠበቁ ያሉ አመራሮችም የሚገኙበት ነው። አድፍጠው የተለያዩ አሻጥሮችን በመስራት የአቢይ አስተዳደር በኦሮሚያ ላይ እንዳይረጋጋ የሚያደርጉ ተግባራትን ይወጣሉ። ይህንን ስራቸውንም በጸጥታ መዋቅሩ ውስጥ ለማስገባት እንቅስቃሴዎችን ያደርጋሉ። እነዚህ አካላት በነጃዋር መታሰር ከፍተኛ ቅሬታ ውስጥ የገቡ እንዳሉ ይታወቃል። የነጃዋር እና ለማ ደጋፊ የሆኑና በጸጥታ ተቋማት ውስጥ የሚገኙ በርካታ ግለሰቦች እንዳሉ የሚታወቅ ሲሆን እነዚህ አካላት የአቢይ አስተዳደር ተረጋግቶ ክልሉን ሆነ ሃገሪቷን በሚገባ እንዳያስተዳድር የተለያዩ

አሻጥሮችን የመስራት አቅም ያላቸው ናቸው። የአብይ አስተዳደር ለነፍጠኛው ያደረና የሚያደላ ነው የሚል ምልከታ ያላቸው እስከ ታችኛው መዋቅር ድረስ ያሉ የኦሮሚያ ባለስልጣናት አሉ። እነዚህ አካላት የአብይን አስተዳደር ከማዳከምና በኦሮሚያ ላይ የሚንቀሳቀሱ የተለያዩ ሃይሎችን ከመደገፍ ወደኋላ የማይሉ ናቸው። በተለይ የኦሮሚያ ክልል ከአማራ ክልል ባለስልጣኖች ጋር የሚገባውን እሰጠገባ በከፍተኛ ሁኔታ ይፈልጉታል። ይህንንም ክልሉ ተረጋግቶ እንዳይቀመጥ ለማድረግ ይጠቀሙበታል።

በኦሮሚያ ውስጥ የኦነግ ሸኔ እየተጠናከረ መምጣትን በበጎ የሚመለከቱ ወይም የሃይል ሚዛን ያስጠብቅልናል ብለው የሚያምኑ እስከ ታችኛው መዋቅር ድረስ ያሉ የኦሮሚያ ክልል ባለስልጣነት ይገኛሉ። እነዚህ የመንግስት አካላት የአቢይ አስተዳደርን የሚቃወሙ ወገኖችን ሲደግፉና ሲያበረታቱ ይታያሉ። የኦነግ ሸኔ በተለያዩ ቦታዎች የሚወስዳቸውን እርምጃዎች መረጃዎችን በማቅረብ የሚደግፉ እንዳሉ ሊታወቅ ይገባል። በአጠቃላይ በኦሮሚያ ክልል ያለው የመንግስት መዋቅር የተረጋጋ ያልሆነና ለሌሎች አካላት መጠቀሚያ የመሆን እድሉ ሰፊ መሆኑ ክልሉን ለማናጋት ለሚፈልጉ ሃይሎች የተመቸ አድርጎታል። ይሄም የብሄራዊ ደህንነት ስጋት የሚጭር ሁኔታን እየፈጠረ እንደሆነ ሊታወቅ ይገባል።

### 1.4. ጽንፈኝነት

በአገራችን በአሳሳቢ ደረጃ እየተስተዋሉ ከሚመጡ ችግሮች ውስጥ ጽንፈኝነት ተጠቃሽ ነው። በተለይ የሃይማኖት እና የዘውግ ጽንፈኝነት በተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች እየታዩ መምጣታቸው ብሄራዊ የደህንነት ስጋት ወደ መሆን ተሸጋግሯል። ከሃይማኖት ጽንፈኝነት ጋር ተያይዞ በተለይ የእስልምና አክራሪነት በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች እንዲስፋፋ በማድረግ ፍላጎታቸውን (interest) ለማሟላት የሚደረግ ጥረት አለ። የእስልምና አክራሪነትን በእምነቱ ተከታዮች ላይ በማስረጽ ለፖለቲካዊ ፍጆታ የማዋል እንቅስቃሴዎች ይታያሉ።

በእስልምና አክራሪዎች ቀስቃሽነት የእስልምና እምነት ተከታዮች በሚበዙበት የተለያዩ ቦታዎች ላይ የአክራሪ አስተምህሮትን በወጣቱ ላይ በማስረጽ በፖለቲካ እንቅስቃሴ ውስጥ በንቃት የሚሳተፉበትን ሁኔታ እየፈጠሩ ይገኛሉ። በአገሪቱ ላይ የሚቀሰቀሱ የተለያዩ ቀውሶችን ከማባባስ አልፎ እራሳቸውም የሚሳተፉበትን ሁኔታ በመፍጠር የተጽኖ አድማሳቸውን ያሰፋሉ። በዚህ ሂደት ውስጥ የሚሰማሩ በርካታ አካላት ያሉ ሲሆን መረባቸውን በመዘርጋት እርስ በርስ በመናበብ ስራዎችን ያከናውናሉ። በዚህ መረብ ውስጥ በተለያዩ ከተሞች የሚኖሩ ባለሃብቶችንም ያቀፈ ሲሆን እንቅስቃሴዎችን የሚያደርጉት በዋናነት መስጊድን መከለያ በማድረግ ሲሆን የተለያዩ የግለሰብ መኖሪያ ቤቶች፣ ሆቴሎች፣ መሰብሰቢያ አዳራሾችና በመጋዘኖች (አብዛኛው ስብሰባም ሆነ ሴራ እዚህ ውስጥ ይካሄዳል) ላይም ያደርጋሉ። ውጪ አገራት ካሉ ከተለያዩ ወግ አጥባቂ ከሚባሉት የሙስሊም ወንድማማች ማህበራት ጋር የጠበቀ ግንኙነት አላቸው። በተለይ ከግብጽ፣ ሳውዲአረቢያና ኳታር የቀረበ ወዳጅነት እንዳላቸው ይታመናል። የገቢ ምንጫቸው ከውጭ በሚላኩ ብሮች፣ ከህገወጥ ኮንትሮባንድ በሚገቡ ሸቀጣ ሸቀጦች፣ በውድ መአድናት ሽያጭና ከመንግሥት እውቅና ውጪ የሆነ ብር የማግኛ ዘዴዎች ነው።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ አይሲአይስ (ISIS)፣ አልቃይዳ እና አልሻባብ በሀገራችን እግራቸውን ለመትከል ሰፊ እንቅስቃሴ እያደረጉ ይገኛል። እነዚህ አካላት በሀገር ውስጥ ያሉ የእስልምና አክራሪነትን በሚያቀነቅኑ ሰዎች አማካኝነት መሰረታቸውን እንዳይጥሉ የጸጥታ አካላት ከፍተኛ ክትትል ማድረግ ይኖርባቸዋል። አይሲአይስ (ISIS) ወጤታማ የምልመላ ስራዎችን እያከናወነኩ ነው እስከማለት ያደረሰው ዝም ብሎ ባዶ ፕሮፓጋንዳ ነው ብሎ መዘናጋት አያስፈልግም። በተለይ በቅርብ ጊዜ እየተከሰቱ ያሉ

ሃይማኖት ተኮር ግጭቶችን የማባባስና ይህን ተከትሎ የእምነቱ ተከታዮችን በእምነቱ ተቆርቋሪነት ሰበብ ወደ ጽንፈኝነት እንዲገቡ የማድረግ ስልቶችን ነድፈው እየተንቀሳቀሱ እንደሆነ ግንዛቤ ሊወሰድ ይገባል።

በሌላ በኩል የክርስትና በተለይ የኦርቶዶክስ ክርስትና እምነት አክራሪነት እየተስፋፋ እየመጣ እንደሆነ ሊታወቅ ይገባዋል። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የኦርቶዶክስ ክርስትና እምነት በተለያየ አቅጣጫ የጥቃት ኢላማ ተደርጋለች የሚለው እሳቤ በበርካታ የእምነቱ ተከታዮች ዘንድ እየተቀነቀነ ይገኛል። ይሄም የኦርቶዶክስ ክርስትና እምነት አክራሪነትን ሊወልድ እንደሚችል ግንዛቤ መውሰድ ያስፈልጋል። የኦርቶዶክስ ክርስትና እምነት አክራሪነት እምነቷን ከጥቃት ለመከላከል በሚል ምእመኑን ሊያሰባስብ ይችላል። በተለያዩ የኦሮሚያ ክልል ቦታዎች የኦርቶዶክስ እና የእስልምና እምነት ተከታዮች መካከል በየጊዜው የሚነሳው ግጭት እንደማሳያ ሊወሰድ ይገባዋል። የኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች መንግሥት ቤተክርስቲያናን ከጥቃት ሊከላከል አልቻለም የሚል አመለካከት ይዘዋል። እየደረሰ ላለው ጥፋት መንግስትን ተጠያቂ እያደረጉ ይገኛሉ። ይሄም የእምነቱ ተከታዮች እምነቱን ማእከል አድርጎ ወደ መደራጀትና እራሳችንን በራሳችን እንከላከላን ወደሚል አካሄድ ሊሄድ እንደሚችል ግምት መውሰድ ያስፈልጋል። እንደዚህ ዓይነት  እምነት ተኮር የሆኑ አደረጃጀቶች የሚፈጠሩ ከሆነ ሀገሪቷን ወደ ጥፋት ሊወስድ ወደ የሚችል የሃይማኖች ግጭትን የሚያስፋፋ አካሄድ ሊሄድ የሚችልበት እድል እንዳለ ሊታመን ይገባል። በተለይ በቅርቡ የተፈጠሩት እናት ፓርቲ እና ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ እምነት ተኮር በመሆናቸውና የሃይማኖት ጽንፈኝነትን ፖለቲካዊ ቅርጽ እንዲይዝ የማድረግ አቅም ያላቸው በመሆኑ የብሄራዊ ደህንነት ስጋት ደረጃ ውስጥ ሊካተቱ ይገባል። ፖለቲካዊ ቅርጽ ያለው የሃይማኖት ጽንፈኝነት ሃገሪቷን ወደ ትርምስ እንዳይከት ከፍተኛ ጥንቃቄ የሚሻ ጉዳይ ነው። አንዴ ከእጅ ካመለጥ መመለስ ወደ የማይቻልበት ደረጃ ሊሄድ ስለሚችል እምነት ተኮር ሆነው የተቋቋሙ የፖለቲካ ድርጅቶችን በቅርበት መከታተል ያስፈልጋል።

የዘውግ ጽንፈኝነት በተለይ በኦሮሚያ እና አማራ ክልል እየተስፋፋ ይገኛል። የዘውግ ጽንፈኝነትን ለፖለቲካ የስልጣን መወጣጫ አድርገው የሚጠቀሙ አካሎች በስፋት እየተፈጠሩ ነው። ወጣቱ ይህን ጽንፈኝነት እንዲያራግብ እና መንግሥት ላይ ተጽኖ በማድረግ የሚፈልጉትን የፖለቲካ አላማ ለማሳካት ይጥራሉ። በዚህ ሂደት ላይ በመንግሥት መዋቅር ውስጥ የሚሰሩ አካላት የዘውግ ጽንፈኞችን የሚደግፉበት ሁኔታ እየተፈጠረ መሆኑ ችግሩን የበለጠ ውስብስብ ያደርገዋል።

በኦሮሚያ ክልል በተለያዩ አክቲቪስቶች፣ የፖለቲካ ድርጅቶች፣ ታዋቂ ሰዎች እና ባለሃብቶች ጭምር ድጋፍ እየተደረገለት ያለው የኦሮሞ ጽንፈኛ ብሔርተኝነት መሰረቱን እንዲያሰፋ እየተደረገ ነው። የሚዲያ ድጋፍም ይደረግለታል። በማህበራዊ ሚዲያም ከፍተኛ ዘመቻ እየተደረገ እንደሆነ ይታወቃል። ዋና አላማውም የክልሉ ገዢ የሆነውን የኦሮሚያ ብልጽግና እና ጠ/ሚኒስተር አቢይን ከስልጣን ላይ ከማውረድ ጀምሮ ኦሮሚያ የሚባል ሀገር እስከመፍጠር የሚዘልቅ ነው። ይህ የማይሳካ ከሆነ ብዙ ሙብት ያለው ኮንፌዴሬሽን ለመፍጠር ያለመ ነው። ይህንን ዓላማ ለማስፈጸም ከሰላማዊ እንቅስቃሴዎች ባሻገር የአመጽ እና የጉልበት ተግባራትን ለመፈጸም የሚያስችል አደረጃጀቶችን ለመፍጠር የሚደረግ ሙከራ አለ። የኦነግ ሸኔ እንቅስቃሴ አንዱ የዚህ አካል መሆኑን ልብ ማለት ያስፈልጋል። በተለያዩ የኦሮሚያ አካባቢዎች ማንነት መሰረት አድርጎ የሚወሰዱ ጥቃቶች የዚህ የዘውግ ጽንፈኝነት ትሩፋቶች ናቸው።

በአማራ ክልል የሚታየው የዘውግ ጽንፈኝነት አማራው ተጠቅቷ፣ ተፈናቅሏል፣ የሚገባውን ጥቅም አላገኘም እንዲሁም በአማራ ሕዝብ ቁመት ልክ የሆነ በፌደራሉ መንግሥት ላይ ስልጣን የለውም ወዘተ የሚሉ አጀንዳዎችን ማእከል አድርጎ የሚቀነቀን ነው። ለአማራው ያልሆነች ኢትዮጵያ ለኛ ምናችንም አይደለችም የሚል ቅስቀሳ ሲደረግ ተስተውሏል። የአማራ ጽንፈኛ ብሄርተኝነትን በአብን (የአማራ ብሄራዊ ንቅናቄ) ዙሪያ በማምጣት ድርጅታዊ ቅርጽ እንዲኖረው ለማድረግ እየተሞከረ

ይገኛል። በክልሉ የመንግሥት መዋቅር ውስጥ የሚሰሩ የተወሰኑ ባለስልጣናት ሳይቀሩ የዚህ ጽንፈኝነት አቀንቃኝ የሆኑበት አግባብ አለ። የአማራ ጽንፈኛ ብሄርተኝነት ዋና አላማው በኢትዮጵያዊነት የሚታወቀውን የክልሉን ሕዝብ ወደ አማራ ብሄርተኝነት አቀንቃኝነት ስር እንዲሰለፍ ማድረግ ነው። ኢትዮጵያ ለአማራው የማትሆን ከሆነ አማራ የሚባል ሃገረ መንግሥት በመመስረት የራሳችንን እድል በራሳችን እንወስናለን የሚሉ ሁሉ የተፈጠሩበት ነው። በአሁን ሰአት ይህንን አባባል ከአንዳንዶቹ የጽንፈኛ ብሄርተኝነት አቀንቃኞች በስተቀር ሌሎች በስፋት ሲያነሱት አይታዩም። የታጠቀ የአማራ ሰራዊት ለማቋቋም የሚደረገው ጥረት አንዱ ከዚህ የአማራ የጽንፈኛ ብሄርተኝነት ስር እንዲሰድ ከማድረግ ጋር የተያያዘ እንደሆነም ግንዛቤ ሊኖር ይገባል።

ባጠቃላይ የሃይማኖት እና የዘውግ ጽንፈኝነት ብሄራዊ የደህንነት ስጋት እየሆነ መጥቷል።

1.5. የደህንነት ማህበረሰብ እና የጸጥታ ተቋማት አቅም ደካማነት

የደህንነት ተቋማት የተለያዩ ጥቃቶች እና ግጭቶች ከመከሰታቸው አስቀድሞ እነዚህን ጥቃቶች እና ግጭቶች ማስቀረት የሚያስችል የተተነተነ መረጃ የማቅረብ አቅም ደካማ መሆን በሰፊው ይስተዋላል። በተለይ የትንበያ መረጃ ትንተና ደካማ መሆን እየተፈጠሩ ካሉ የደህንነት ስጋቶችና አደጋዎች እንጻር ስናየው የድክመት ደረጃው በደንብ እንዲታይ ያደርገዋል። የብሄራዊ የደህንነት ስጋቶችን ለመከላከል በሚመጥን ደረጃ የመረጃ እና ደህንነት ተቋማት በሚጠበቅባቸው ልክ ዝግጁ አለመሆናቸው ሃገሪቷ ከፍተኛ ችግር ውስጥ እንዳለች ያሳያል።

የመረጃ እና ደህንነት ተቋማት ለስርገት የተጋለጡ በመሆናቸው በተቋማቱ ውስጥ የህወሃት እና የኦነግ የነቁ እና የተኙ ወኪሎች (active and sleeper cell) እንቅስቃሴዎችን ሊያደርጉ የሚችሉበት እድል ሰፊ ያደርገዋል። ይሄም የሃገሪቷን ደህንነት አቅም እንዲመቻመች የማድረግ እድልን ይፈጥራል። በመሆኑም የደህንነት ማህበረሰቡ ከፍተኛ ትኩረት አግኝቶ መዋቅራዊ ማሻሻያዎችን በፍጥነት ማድረግ ካልቻለ ሃገሪቷ ለከፍተኛ አደጋል እንድትጋለጥ የማድረግ አቅሙ ከፍተኛ ነው። የመረጃ ውድቀት በተደጋጋሚ እየተከሰተ መሆኑ የሃገሪቷን ተጋላጭነት ያሰፋ አድርጎታል።

2. የውጪ ተጨባጭ የደህንነት ስጋቶች

በርካታ የውጭ ተጨባጭ ደህንነት ስጋቶች ያሉባት ሃገር ናት ኢትዮጵያ። በተለይ በቅርብ ጊዜ ከፍተኛ እና የተቀናጀ የውጭ ተጨባጭ የደህንነት ስጋቶች እየተስተዋሉ ይገኛሉ። ዋና ዋና የሚባሉትን የውጪ የደህንነት ተጨባጭ ስጋቶች እንደሚከተለው ይቀርባል፦

2.1. ግብጽ የፈጠረችው ስጋት

ግብጽ ከህዳሴ ግድብ ጋር ተያይዞ በኢትዮጵያ ብሄራዊ ጥቅሞች እና ደህንነት ላይ ከፍተኛ አደጋ ደቅናለች። በአለም አቀፍ ተቋማት ዘንድ ያላትን ተቀባይን በመጠቀም ሰፊ ዘመቻ እያደረገች እንደሆነ ይታወቃል። በኢትዮጵያ በኩል ይህንን የግብጽ ዘመቻ ለመቋቋም የሚደረጉ ጥረቶች እንዳሉ ቢታወቁም በሚፈለገው ልክ በቂ አይደለም። በተለይ የውጪ መረጃ ተቋም በእንደዚህ አይነት ጊዜ ከፍተኛ ሚናውን መወጣት ሲገባው እዚህ ግባ የሚባል እንቅስቃሴ እያደረገ አይደለም። ግብጽ በግላጭም ሆነ በስውር ኢትዮጵያ ላይ ተጽኖ የሚያሳድር እንቅስቃሴዎችን እያደረገች ነው። በኢትዮጵያ በኩል ይህንን ከግብጽ የሚመጣን ተጽኖ ለመቋቋም ብሎም ወደ አጥቂነት ለመሸጋገር በስውር የሚደረጉ ኦፐሬሽኖችን (covert operations) የመስራት አቅም ደካማ መሆን የበለጠ ተጋላጭነት እያደረጋት ይገኛል።

ግብጽ በሰሜን ሱዳን የመንግስት መዋቅር እንዲሁም በወታደራዊ እና ደህንነት ውስጥ ያሉ ከፍተኛ ባለስልጣናትን በመያዝ ኢትዮጵያ ላይ የተቀናጀ እንቅስቃሴዎችን እያደረገች ትገኛለች። ይህ እንቅስቃሴ ደቡብ ሱዳን ድረስ በመዝለቅ ኢትዮጵያን ተጽኖ ውስጥ እንድትገባ የሚያሳድሩ እንቅስቃሴዎች እያደረገች ለመሆኑ የሚያሳዩ መረጃዎች አሉ። በተለይ በኢትዮጵያ ውስጥ ያለመረጋጋት እንዲፈጠር የሚያደርጉ እንቅስቃሴዎችን በሰሜን እና ደቡብ ሱዳን ውስጥ በግብጽ በሚደገፉ ቡድኖች አማካኝነት ለማድረግ እና ኢትዮጵያ ውስጥ ካሉ ሃይሎች ጋር ለማቀናጀት እየሰራች ስለመሆኑ ፍንጭ የሚሰጡ ጥሬ መረጃዎች አሉ። ባጠቃላይ ግብጽ የውጪ የደህንነት ተጨባጭ ስጋት መሆኗ ላይ ጥያቄ አይነሳም።

2.2. ሰሜን ሱዳን የፈጠረችው ስጋት

ሰሜን ሱዳን የድንበር ይገባኛል ጥያቄ ጋር ተያይዞ የብሄራዊ ደህንነት ስጋት መሆኗ አይቀሬ አድርጎታል። ኢትዮጵያ ተዳክማለች የሚል እይታ ያላት ሱዳን ከድንበር ጋር በተያያዘ በተደጋጋሚ የምታነሳውን ጥያቄ በሃይል ጭምር በመታገዝ ፍላጎታን ለማሳካት የሄደችበት እርቀት ሲታይ ሰሜን ሱዳንን በቅርበት መከታተል አንዱ ዋነኛ ጉዳይ አድርጎታል። ሰሜን ሱዳን እንዲህ በሃይል ፍላጎቷን ለማሳካት የሄደችበትን እረቀት የኢትዮጵያ የመረጃ እና ደህንነት ተቋማት ቀድመው በመረጃ መተንበይ አለመቻላቸው ሃገሪቷን ለደህንነት ተጋላጭነት እንድትዳረግ የእራሳቸውን ሚና ተወጥተዋል።

ከሰሜን ሱዳን ጋር ተያይዞ የሚነሳ ችግሮች ከህወሃት ጋር የተፈጠረውን የጦርነት ሂደቶች የበለጠ ውስብስብ የማድረግ አቅም ያለው በመሆኑ የሰሜን ሱዳንን ሁኔታ ችላ ማለት ፈጽሞ የሚገባ አይደለም። በኢትዮጵያ በኩልም የተጠናና የተቀናጀ የኢትዮጵያን ጥቅም እና ደህንነት የሚያስጠብቅ ስውር እንቅስቃሴዎች ማድረግ እንደሚያስፈልግ ጥያቄ ውስጥ የሚገባ አይደለም።

የሰሜን ሱዳን የወታደራዊ እና ደህንነት ከፍተኛ ባለስልጣናት በቤንሻጉል ጉምዝ ክልል የሚፈጠሩ ችግሮች ላይ እጃቸው ያለበት መሆኑ እና አካባቢውን እነሱ በሚፈልጉት መንገድ ተጽኖ ውስጥ ለማስገባት እንቅስቃሴ እያደረጉ እንዳለ የሚያሳዩ መረጃዎች አሉ። ይህንን የሰሜን ሱዳን እረጅም እጅ መልክ ማስያዝ የመንግስት ሃላፊነት መሆኑን እዚህ ላይ በማሳወቅ መንግስት ድንበር ተሻጋሪ የሆኑ ጉዳዮች ያሉት መሆኑን አምኖ በሚፈለገው ልክ መንቀሳቀስ ይኖርበታል። ባጠቃላይ ከሰሜን ሱዳን ጋር የሚያዋስኑ ድንበሮች አካባቢ የሚደረጉ እንቅስቃሴዎችን በቅርበት መከታተል ያስፈልጋል። ሰሜን ሱዳን የኢትዮጵያ ብሄራዊ ደህንነት ስጋት እየሆነች መምጣታ ላይ ምንም አይነት ብዝታ ሊኖር አይገባም።

**ክፍል ሁለት፡ የምርጫ ደህንነት**

ኢትዮጵያ ብሄራዊ የምርጫ ሂደት ውስጥ ትገኛለች። ይህ የምርጫ ሂደት ሃገሪቷን ወደ ሰላማዊ የስልጣን ችግግር ሂደት ውስጥ ይከታታል ተብሎ ቢታሰብም በበርካታ እና ውስብስብ ችግሮች የታጀበ የምርጫ ሂደት እየተከናወነ ነው። በቀጥታ ይሁን በተዘዋዋሪ ከላይ የተቀመጡት የብሄራዊ ደህንነት ስጋቶች በምርጫው ሂደት ላይ የራሳቸውን ተጽኖ ያሳርፋሉ። የምርጫ ሂደቱ ሃገሪቷን አዎንታዊ ወደ ሆነ ሰላማዊ የስልጣን ሽግግር በመውሰድ የዴሞክራሳዊ ሂደቱን የተሳለጠ የማድረግ አቅም እንዳለው ሁሉ ሃገሪቷን ወደ ሌላ የቀውስ ሂደት ውስጥም ይጇት ሊገባ እንደሚችል ትንበያዎች ይቀርባሉ። ከላይ ከተቀመጡት የብሄራዊ ደህንነት ስጋቶች እና ሌሎች ችግሮችን መነሻ በማድረግ ከምርጫ ጋር ተያይዞ የሚነሱ ጉዳዮች ለሌላ አላስፈላጊ ቀውስ ሃገሪቷን ሊዳርጋት የሚችልበት እድል እንዳለ መገንዘብ ያስፈልጋል። ሃገሪቷ በዘርፈ ብዙና ውስብስብ ችግሮች የተተበተበች በመሆኑ ይህ የምርጫ ሂደት እነዚህ ችግሮች በማጉላት ውጥረት ውስጥ ሊያስገባ የሚችልበት እድል እንዳለ የሚያሳዩ ምልክቶች አሉ።

ይህም እንዳለ ሆኖ፤ የምርጫ ሂደቱ ሚዛናዊ እና በመሰረታዊነት ቅብሉነት ያለው መንግስት መመስረት የሚያስችል የምርጫ ሂደት ከተካሄደ ደግሞ የሃገሪቷ ተስፋም ጭምር ነው።

ጠቅለል ባለ ሁኔታ ሲታይ በምርጫው ሂደት ላይ ሁለት ቡድኖችን ማየት ይቻላል። አንደኛው የተሳካ ምርጫ እንዳይካሄድና የምርጫውን ታእማኒነት ጥያቄ ውስጥ ለመክተት የሚንቀሳቀሱ ሃይሎች ሲሆን ሌላኛው ቡድን በምርጫው ተስፋ ያደረገ እና በሚፈለገው ደረጃ እንኳን ባይሆን መሰረታዊ በሚባል ደረጃ ቅቡልነት ያለው መንግስት ምፍጠር ከተቻለ የምርጫውን ሂደት እንደስኬት ሊቆጠር ይገባል የሚሉ ናቸው። እነዚህ ሰፊ ማእቀፍ ያላቸው ቡድኖች የምርጫውን ሂደት ላይ በአዎንታዊ እና በአሉታዊ ሁነት ምርጫውን ላይ ተጽኖ የሚያሳድሩ ናቸው። ሁለቱን ቡድኖች በተወሰነ መልኩ ለማየት እንሞክራለን።

የመጀመሪያው ቡድን የምርጫውን ታእማኒነት ጥያቄ ውስጥ ለመክተት የሚሰራ ቡድን ነው። ይህ ቡድን በዋናነት የመንግስትን ስልጣን በሃይል ለመያዝ የሚንቀሳቀስ ቡድኖች ያሉበት ሲሆን እንደ ኦነግ ሸኔ፣ ህወሃት የመሰሉ ድርጅቶች ይገኙበታል። በሌላ በኩል በተለያየ ምክንያት በምርጫው የማይሳተፉ ድርጅቶችም እንደ ኦፌኮ፣ ኦነግ የመሳሰሉት ይገኙበታል። የዚህ ቡድን ፍላጎት የምርጫው ታእማኒነት ጥያቄ ውስጥ እንዲገባ የማድረግ ብቻ ሳይሆን የአቢይ አስተዳደር ሃገሪቷን በአግባቡ መምራት እንዳልቻለ ለማሳየትም የሚደረግ እንቅስቃሴ ነው። ባጠቃላይ የመንግስት አስተዳደር እና የምርጫ ሂደቱ የታእማኒነት ጥያቄ እንዲነሳበት በማድረግ አጠቃላይ የፖለቲካ አቅጣጫው ላይ ተጽኖ ፈጥሮ እነሱ ወደ የሚፈልጉት የፖለቲካ ሂደት ውስጥ እንዲገባ ነው እየሰሩ ያሉት። ይህን እንቅስቃሴ የሚፈጽሙት ደግሞ በተለያየ መልክ ሲሆን ከሰላማዊ የፕሮፓጋንዳ ስራ ጀምሮ ሃይልን እስከመጠቀምና ነጹሃንን እስከመግደል የሚደርስ መንግስት ሃገሪቷን መቆጣጠር እና የዜጎችን ደህንነት መጠበቅ የሚችል አይደለም የሚለውን መልእክት እንዲሰራጭ በማድረግ ህዝቡ በመንግስት ላይ የሚኖረውን እምነት እንዲሸረሽር የሚያደረግ ስራ ነው። በዚህም ሂደት ከተቻለ ምርጫው እንዲደናቀፍና እንዳይደረግ ወይም እንዲራዘም ለማድረግ ሲሆን ምርጫ የሚደረግ ከሆነ ደግሞ የሚመጣው መንግስት የቅቡልነት ችግር ያለውና ደካማ መንግስት እንዲሆን ታልሞ የሚፈጸም ድርጊቶች ናቸው። በዚህ እንቅስቃሴ ውስጥ በመንግስት መዋቅር ውስጥ ያሉ የመንግስት አመራሮች የሚሳተፉበትና እገዛ የሚያደርጉበት ሁኔታ እንዳለ መታወቅ አለበት። ይህ ሂደት ከተቻለ እስከ መፈንቅለ መንግስት ድረስ እንዲያድግ ለማድረግ የሚሰራበትና አሁን ያለውን የአቢይ አስተዳደር በሃይል ለማውረድ ጭምር እንቅስቃሴዎች የሚደረጉበት ነው።

ሁለተኛው ቡድን መሰረታዊ በሚባል ደረጃ ቅቡልነት ያለው የምርጫ ሂደት ከተፈጠረ ለዴሞክራሲያዊ ሽግግሩ ወሳኝ እንደሆነ የሚያምነው ቡድን ነው። በዚህ ቡድን ውስጥ ኢዜማ እና ብልጽግና በዋናነት የሚካተቱ ናቸው። ይህን አካሄድ ኢዜማ ሙሉ ለሙሉ አቋሙ አድርጎ ሲቀበለው የሚታይ ሲሆን በብልጽግና በኩል እንደ ፓርቲ የሚቀበሉት ቢሆንም በብልጽግና ውስጥ ያሉ አካላት ግን ይህ አካሄድ የአቢይን አስተዳደር እንዲቀጥል የሚያደርግ ስለሆነ የመጀመሪያውን ቡድን እንቅስቃሴ በመደገፍ የአቢይን አቅም እና ከኢዜማ ጋር ተኩኖ የአንድነት ሃይሉን ለማጠናከር የሚረዳቸው በመሆኑ ቀጣይ የሚኖረውን መንግስት የተረጋጋ እንዳይሆን የሚያያደርጉ ስራዎችን የሚሰሩ የብልጽግና አካላት እንደሚኖሩ መታወቅ አለበት። እነዚህ የብልጽግና አመራሮች አቢይ ስልጣኑን የሚያደላድል ከሆነ በእሱ የአመራር ክበብ ውስጥ ቦታ አይኖረንም እና ጥቅማችንን ማስጠበም አይቻለንም ብለው ከአሁኑ የሚያስቡ አካላት እንደሆኑ ልብ ሊባል ይገባል።

በሌላ መልኩ ደግሞ እንደሶስተኛ ቡድን የሚቆጠሩት ከላይ ከተቀመጡ ቡድኖች ጋር ተያይዞ የሚነሱ ጉዳዮችን እንደየሁኔታው በመጠቀም የፖለቲካ ፍላጎታቸውን ለማሳካት የሚያሰሉ አካላት ያሉበት ቡድን ነው። በዚህ ቡድን ውስጥ አብን፣ እናት እና ነጽነት እና እኩልነት በዋናነት ይጠቀሳሉ።

ባጠቃላይ ሃገሪቷ አሁን ካለችበት ዘርፈ ብዙ ችግሮች አንጻር የምርጫው ሂደት በብዙ ውስብስብ ችግሮች የሚታጀብ በመሆኑ የምርጫውን ሂደት እንዳይበላሽ የሚያደርጉ ዘርፈ ብዙ ስራዎችን መስራት የሚያስፈልግበት ጊዜ ነው። በተለይ የምርጫ ቦርድ የአቅም ውስኑነት የምርጫውን ሂደት ላይ አሉታዊ ተጽኖ የማሳደር አቅሙ ከፍተኛ በመሆኑ ወደ ሌላ ቀውስ ሊያመራ የሚችልበት እድልን ይፈጥራል። ስለዚህ የምርጫ ቦርድ መሰረታዊ የሚባሉ የምርጫ መመዘኛዎችን ከማማላት አንጻር ክትትል ሊደረግበት ይገባል። በተለይ የምርጫ ቦርድ የአቅም ውስኑነቱ እንዲሰፋ የሚያደርጉ የአሻጥር እንቅስቃሴዎች ሰለባ እንዳይሆን ከፍተኛ የደህንነት ክትትል የሚያስፈልገው ተቋም ነው።

ከምርጫ ደህንነት ጋር ተያይዞ የሚነሳው ሌላው ወሳኝ ነጥብ በመንግስት መዋቅር ውስጥ ያሉ አካላት እንሸነፍበታለን ብለው በሚያስቡት ቦታዎች ላይ ምርጫውን ለማጭበርበር የሚያስችል ፍላጎቶች እንዳሉ ጥሬ መረጃዎች ያሳያሉ። በተለይ በገጠራማ አካባቢ ታእማኒነት ያለው ምርጫ ቢደረግ እንሸነፋለን ብለው የሚሰጉ የብልጽግና ተመራጮች የምርጫ ታእማኒነትን ጥያቄ ውስጥ በሚከት ደረጃ እንቅስቃሴዎችን ለማድረግ እየተዘጋጁ እንደሆነ የሚጠቁሙ ጥሬ መረጃዎች አሉ። እንደዚህ አይነት እንቅስቃሴዎች በምርጫው ሂደት ላይ የሚያሳድረው አሉታዊ ተጽኖ ከፍተኛ በመሆኑ ከምርጫ ሂደት ጋር ተያይዞ ለሚነሱ ውዝግቦች እና ቀውስ ምክንያት የመሆን እድሉ ሰፊ ነው።

በሌላ በኩል የመራጮች ምዝገባ አነስተኛ መሆን ከምርጫ ሂደት በኋላ የሚመሰረተውን መንግስት ቅቡልነት ክፉኛ የሚጎዳው በመሆኑ መራጮች ለምን መመዝገብ አልፈለጉም የሚለው ጥያቄ በአጣጋቢ መልኩ መመለስ ያስፈልጋል። በተቀናጀ መንገድ ህዝቡ እንዳይመርጥና የምርጫ ካርድ እንዳይወስድ የሚደረጉ ቅስቀሳዎች እንዳሉ ይታወቃል። በብልጽግና ካድሬዎች ተጽኖ አይመርጠንም ብለው የሚያስቡት ማህበረሰብ የምርጫ ካርድ እንዳይወስድ የተቀነባበረ ዘመቻ ሲያደርጉ የሚታይባቸው አካባቢዎች አሉ። በሌላ በኩል የምርጫ ታእማኒነት እንዳይኖር የሚፈልጉ ሃይሎችም ህዝቡ ምርጫ ላይ እንዳይሳተፍ ቀስቀሳዎችን እያደርጉ ይገኛሉ። በተለይ በኦሮሚያ እንደዚህ አይነት ቅስቀሳዎች በሰፊው ይስተዋላሉ። ባጠቃላይ የመራጮች ምዝገባ እና ምርጫ የሚያካሂደው የሰዎች ብዛት ከምርጫ ቅቡልነት ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያለው በመሆኑ በዚህ ጋር የተያያዙ የሚያጋጥሙ ችግሮች የደህንነት ስጋት ተደርገው ሊወሰዱ የሚችሉበትን እድል እንዳለ መታወቅ አለበት።

ከምርጫ ቦርድ ጋር ተያይዞ የሚፈጠሩ ችግሮችና የአቅም ውስኑነት ሃገሪቷን የምርጫ ቀውስ ውስጥ ሊከታት የሚችልበት እድል እንዳለ በማመን ይህ ጉዳይ የብሄራዊ ደህንነት ስጋት ከመሆኑ በፊት የተቀናጀ ዝግጁነት መፍጠር የሚያስችል ስራዎችን ከአሁኑ መስራት ያስፈልጋል። በዚህ ሂደትም የተፎካካሪ ፓርቲዎች የሚጠበቅባቸውን ሚና መወጣት ይኖርባቸዋል።

**ክፍል ሶስት፡ ኢዜማ ሊከተላቸው የሚገባቸው ከብሄራዊ ደህንነት ጋር የተያያዙ አቅጣጫዎች**

1. የሃገሪቷ የብሄራዊ ደህንነት ስጋቶች ላይ አመራሮቹ የተሟላ እና ተመሳሳይ ምልከታ እንዲኖራቸው ማድረግ
2. በትግራይ ውስጥ የሚደረጉ የጦርነት ሂደቶች ላይ ተመርኩዞ በተለይ ከኤርትራ ሰራዊት መውጣት ጋር በተያያዘ የኤርትራ ሰራዊት እንዲወጣ የሚጠይቅ አቋም ኢዜማ ማራመድ የለበትም። በአሁን ሰአት የኤርትራ ሰራዊት ከትግራይ የሚወጣ ከሆነ ህወሃት ተመልሶ የበላይነቱን ልዪዝ የሚችልበት እድል እንዳል ያመለክታል። የመከላከያ ሃይል አፋጣኝ በሆነ መንገድ በትግራይ ውስጥ የሚደረጉ እንቅስቃሴዎችን ሙሉ ለሙሉ በቁጥጥር ስር ማድረግ እንዳለበትና የህግ ማስከበሩ ዘመቻ በአጭር ጊዜ አጠናቆ ህዝቡ ሰላማዊ ህይወቱን መኖር የሚችልበትን ሁኔታ እንዲፈጥር እንዲሁም የሰባዊ መብት ጥሰቶች ጋር ተያይዞ ተጠያቂነት እንዲሰፍን ከማሳሰብ ውጪ በአሁን ሰአት

የኤርትራ ሰራዊ በአፋጥኝ ከትግራይ አካባቢ እንዲወጣ መጠየቅ የሃገሪቷን ብሄራዊ ደህንነት የማመቻመች እድሉ ሰፊ እንደሆነ መታወቅ ይኖርበታል።

3. በማንኛውም መልኩ በሃይል መንግስትን ለመገልበጥ የሚደረግ የአመጽ እንቅስቃሴ በጽኑ ሊወገዝ እንደሚገባ ግንዛቤዎች መፍጠር።
4. የዘውግ እና የሃይማኖት ጽንፈኝነትን የሚያመጣውን አደጋ በማመላከት በየጊዜ እንደዚህ አይነት ጉዳዮች ሊወገዙ እንደሚገባ ግንዛቤ መፍጠር
5. ብልጽግና በውስጡ ያሉትን ጽንፈኞች እንዲያጸዳና የተረጋጋ ሃገር ለመፍጠር የሚደረገውን ጥረት አዎንታዊ በሆነ መንገድ እንዲወጣ ተጽኖ ማሳደር።
6. የደህንነት ማህበረሱ አደጋዎች ከመድረሳቸው በፊት ቀድሞ የማስቀረትና የመከላከል ተግባራትን በሚገባ እንዲወጡ የመወትወት እና የብሄራዊ ደህንነት ስጋቶችን ለመከላከል የሚያስችል ዝግጁነት ለመፍጠር መዋቅራዊ የሆነ ለውጥ እንዲፈጥሩ ጫና ማድረግ።
7. ከምርጫ ደህንነት ጋር ተያይዞ ሊነሱ የሚችሉ ችግሮችን ለሚመለከታቸው አካላት በማሳወቅ ትኩረት እንዲያገኝ ማድረግ።
8. ከላይ የተቀመጡት ስጋትቶች አንጻር ኢዜማ እና የኢዜማ አመራር ኢላማ እንደሆኑ ለማሳየት ተሞክሯል። በመሆኑም ኢዜማን እና የኢዜማ ከፍተኛ አመራሮች በተለይ ከፍተኛ የደህንነት ስጋት ካለባቸው ውስጥ ፕ/ር ብርሃኑ ነጋ፣ አቶ አንዷለም አራጌ እና አቶ ክቡር ገና ምርጫው እስኪያልፍ ድረስ በመንግስት የጥበቃ አካላት እንዲጠበቁ ማድረግ የሚቻልበት እድል እንዲኖር መስራት። ካልሆነም ኢዜማ የግል ጠባቂዎችን ሊቀጥር የሚችልበትን ሁኔታ በመፍጠር ደህንነታቸው የተጠበቀ እንዲሆን ማድረግ ይገባል። በሌላ በኩል የኢዜማ ጽ/ቤት ደህንነቱ የተጠበቀ እንዲሆን አስፈላጊው የጥበቃ ቅጥር እንዲከናወንና የደህንነት ካሜራዎች ግዢ ተፈጽመው ስራ የሚጀምሩበት ሁኔታ በፍጥነት መጀምር ያስፈልጋል። እንዲሁም ከፍተኛ የደህንነት ስጋት ያለባቸውን አመራሮች መከታተል የሚያስችል የደህንነት ፕሮቶኮል አዘጋጅቶ ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልጋል።

**ክፍል አራት፡ መንግስት ሊተገብራቸው የሚገቡ ምክረ ሃሳቦች**

1. በትግራይ እና በተለያዩ የኦሮሚያ አካባቢዎች ያሉትን የሽምቅ እንቅስቃሴዎችን ለመቆጣጠር የሚያስችል የጸረ ሽምቅ (counter insurgencies) ስትራቴጂዎችን ቀይሶ ተግባራዊ ማድረግ ይጠበቅበታል። ለዚህ ግዳጅ ብቁ የሆኑ መሆን የሚያስችሉ የተለያዩ አካላት ስልጠናዎችን በመስጠት በዚህ ግዳጅ ላይ ስምሪት እንዲፈጸም ለማድረግ የሚያስችል ዝግጁነት መፍጠር። በመደበኛ የጦርነት ስልት ስልጠና በወሰደ ሃይል የጸረ ሽምቅ እንቅስቃሴ ውጤታማ መሆን ስለማይቻል የጸረ ሽምቅ እንቅስቃሴ በብቃት ለመወጣት የሚያስችል ሃይላትን ማዘጋጀት ያስፈልጋል።
2. የጸረ ህቡዕ እንቅስቃሴዎችን (counter clandestine activities) ለመተግበር የሚያስችል ዝግጁነት በመከላከያ እና በደህንነት ማህበረሱ ዘንድ እንዲፈጠር ማድረግ ያስፈልጋል።
3. የደህንነት ማህበረሰቡ በተለይ የውጪ መረጃ ዘርፍ የስውር ጥቃት እና ኦፐሬሽኖች (covert action and operationስ) መፈጸም በሚያስችል ደረጃ የሙያ ዝግጁነት መፍጠር ይገባዋል።
4. ከላይ ከአንድ እስከ ሶስት የተቀመጡ ተግባራትን ለመፈጸም የሚያስችል የመዋቅር ማስተካከያ ማድረግ የሚያስፈልግ ስለሆነ ተግባራቱን በሚመጥኑ ደረጃ መዋቅሮች ከእንደገና መደራጀት ይኖርባቸዋል።

5. የምርጫ ደህንነትን የሚያመቻምቹ ተግባራትን ለመቆጣጠር የሚያስችል ዝግጁነት የደህንነት ማህበረሰቡ እንዲኖረው ማድረግና የሚፈጠሩ ችግሮችን ተከታትሎ አፋጣኝ እርምጃዎችን በመውሰድ የምርጫ ደህንነትን ማረጋገጥ ያስፈልጋል።
6. የዲፕሎማሲ ስራዎችን ከውጪ መረጃ ስራዎች ጋር እንዲተሳሰሩ አድርጎ ተንካራ የዲፕሎማሲ ዘመቻ በግላጭ እና በስውር ማድረግ ይገባል።
7. ጽንፈኝነትን ለመከላከል የሚያስችል ስትራቴጂዎችን በመንደፍ ተግባራዊ ማድረግ።
8. የምርጫ ደህንነት ከማረጋገጥ አንጻር የተፎካካሪ ፓርቲዎች እና ከፍተኛ አመራሮችን ደህንነት ለማረጋገጥ የሚያስችሉ የጥበቃ ተግባራትን መንግስት እንዲወጣ ማድረግ ያስፈልጋል። ለነዚህ አካላት እንዳለባቸው የደህንነት ስጋት የግል ጠባቂዎችን ጭምር መመደብ ያስፈልጋል።